ያቁሙ

# የኤሮሶል ንክኪ ቅድሚ ጥንቃቄዎች

**ጎብኚዎች** ከመግባታቸው በፊት ከነርስ ጋር ይገናኛሉ።

## ለተፈቀደላቸው ጎብኚዎች ብቻ

*ከመጀምሩ ለመከላከል፣ የጤና እንክብካቤ ሠራተኞች/ ጎብኚዎች እያሉ እቅርታ ከተደረገላቸው፣ ማስክ እንዲያደርጉ ይጠቁ።*

## ከመግባትዎ በፊት፡



እጅዎን ይታጠቡ



ጋዎንና ጓንት ያድርጉ




National Institute for Occupational Safety and Health (NIOSH, ብሔራዊ የሙያ ደህንነት እና ጤና ተቋም) መተንፈሻ ይጠቀሙ (N95/PAPR/CAPR)



የዓይን መጠበቂያ ይጠቀሙ
?ፊት መሸፈኛ ወይም መነጽር ይጠቀሙ

## ሌላ መስፈርቶች፡



በመገልገያ መሣሪያ መመሪያ መሠረት አየርወለድ በሽታ መከላከያ ክፍል (AIIR) ይጠቀሙ።

ሕመምተኛ በሚኖርበት ጊዜ በር ተዘግቶ መቆየት ይኖርበታል አለበለዚያ የሕመምተኛ እንክብካቤ ልጎዳ ይችላል (ለምሳሌ፣ የመውደቅ አደጋ)። ከኤሮሶል የማመንጨት ሂደቶች (AGP) በኋላ በመገልገያ መሠረት ተገቢውን የአየር ዝውውር ጊዜን ይከተሉ።



ለሕመምተኛ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ሊጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ። የጋራ መገልገያዎችን በፀረ ተባይ ያጽዱ።

*ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ በEnvironmental Services (አከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።*

Washington State Hospital Association

07/30/2024

Washington State Department of HEALTH

**ከበር ውጪ ያሳዩ። ታካሚው ከወጣ፣ ክፍሉ ሙሉ በሙሉ ከጸዳ በኃላ ምልክቱን ያንሱ።**

# የኤሮሶል ንክኪ ቅድሜ ጥንቃቄዎች

**ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የተከለከሉ ጉብኚቶች፡ ሠራተኞች በመገልገያ ፖሊሲ መሠረት ለጎብኚዎች ተገብውን ትምህርትና የግል መከላከያ መሣሪያዎች(PPE) መስጠት አለባቸው።**

## የግል መከላከያ መሣሪያዎች (PPE)

***በመደበኛ ቅድመ ጥንቃቄዎች መሠረት ለሎች የግል መከላከያ መሣሪያውች በተጨማሪ፣ በመጀመሪያ ገጽ ላይ የተዘረዘሩትን የግል መከላከያ መሣሪያዎች በመያዝ፣ የሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ለሁሉም የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማሳያዎች ናቸው።***

| *የግል መከላከያ መሣሪያዎች (ልገሳ) ማድረግ።* | ***<u>የግል መከላከያ መሣሪያዎች ማውለቅ</u>*** |
|---|---|
| **1.** የእጅ ንፅህናን ያከናውኑ።<br>**2.** መከላከያ ጋዎን፣ አስተማማኝ የሆነ ጥምጣም/ከረባት ያድርጉ<br>**3.** መተንፈሻ ወይም የፊት ጭምብል ማድረግ፣ ተስማሚና በትክክል መግጠማቸውን ማረጋገጥ።<br>**4.** የፊት መሸፈኛ ወይም መነጽር ይጠቀሙ።<br>**5.** ጓንቶችን ያድርጉ። | **የተጠቀማችሁት CAPR/PAPR ከሆነ፣ በትክክል ለማውለቅ የአምራች አጠቃቀም መመሪያዎችን ይከተሉ።**<br>**1.** ከታካሚ ክፍል ውስጥ ከሆናችሁ፣ እጅን በማይበክል መልኩ ጓንቶችን ያውልቁ።<br>**2.** ጋዎን ያውልቁ - ከረባት/ጥምጣም ይፍቱ፣ ሊጣሉ ለሚችሉ ጋዎኖች ማሰሪያ የሚውል ከሆነ ከረባቱን ይቁረጡ። እያንዳንዱን ክንድ ለማስወገድ አንድ ትከሻን በአንድ ጊዜ በመያዝ ያስወግዱ። ካወለቃችሁ በኃላ በመጠቅለል ትክክለኛ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡ። አሁን ከክፍሉ መውጣት ትችላላችሁ።<br>**3.** እንደወጣችሁ፣ የእጅዎን ንጽሕና (የሚታይ ቆሻሻ፣ የሰገራ ንክኪ ወይም ከቅድመ-ጥንቃቄ መጓደል ንክኪ አጋጥምዎት ከሆነ፣ ሳሙና ውኃ ይጥቀሙ) ያከናውኑ።<br>**4.** የፊት መሸፈኛ/መነጽር ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለሚችል የዓይን መከላከያ መጀመሪያ ክፍል አይንኩ።<br>**5.** መተንፈሻ/የፊት ጭምብል በትክክል በመያዝ ያውልቁ - ተበክሎ ሊሆን ስለምችል የፊት ለፊት ክፍል ከመንካት በመቆጠብ እንዳይበክል አድርገው ተገቢ በሆነ መልኩ ይጣሉ።<br>**6.** የእጅዎን ንፅህና ደጋግመውይጠብቁ። |

**ከሁኔታዎች ጋር ጥቅም ላይ የሚውል እንደ (መገልገያ ፖሊሲ ይመልከቱ) ያሉትን ሁኔታዎችን ለመጠቀም:**

- ኮቪድ-19ን ጨምሮ አዳዲስ የመተንፈሻ አካላት ቫይረሶች
- ኤምፖክስ ቫይረስ

**የታካሚ ምደባ**

- ታካሚን የግል ክፍል ወስጥ ይመድቡ። የማይገኝ ከሆነ፣ ለጋራ መገልገያ መመሪያዎችን ይከተሉ።

**ምግቦችና ዕቃዎች**

- ልዩ ቅድመ ጥንቃቄዎች የሉም። የማዕድ ቤት ዕቃዎች ዕቃ ማጠቢያ ውስጥ ይጠቡ።

**የቆሻሻ እና የአልጋ ልብስ ንጽሕና አጠባበቅ**

- አልጋ ልብስ ከታካሚ ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ ከመጠን በላይ ንክኪና አልጋ ልብስ ማራገፍን ያስወግዱ። ለባዮአዛርድ ቆሻሻ፣ ምድብ ቢ የህክምና ቆሻሻ መመሪያዎችን ይከተሉ።

**ክፍልን ማጽዳት**

- ታካሚው ከወጣ በኃላ ለAIIRs በተቋሙ መመሪያ መሠረት ክፍሉ ተገቢ የሆነ የአየር ዝውውር እንድኖረው በሩን ዘግተው ያቆዩ።
- ተገቢ ከሆነ የአየር ዝውውር በኃላ በሆስፒታሉ አሠራር መሠረት መጋረጃ ቅየራና መደበኛ የጽዳት ሂዴቶች ይካሄዳሉ።

**መሣሪያና አቅርቦቶች**

- ክፍል ውስጥ ያለ አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያና አቅርቦቶችን ብቻ ይጠቀሙ።
- ለታካሚ ብቻ የተፈቀዱ ወይም ልጣሉ የሚችሉ መገልገያዎችን ይጠቀሙ።
- በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ድጋሚ የሚያገለግሉ መሣሪያ/የታካሚ ክፍል ፀር-ተባይ መርጨትና ማጽዳት።

**ትራንስፖርት**

- የታካሚውን የመውጫ ቅድመ ጥንቃቄ ሁኔታ ለተቀባይ ክፍል ማሳወቅ።
- ታካሚው እጁን መታጠብ አለበት። ታዞላቸው ከሆነ፣ የቀዶ ጥገና ጭምብል ያድርጉ።
- አጓጓዡ ከታካሚው ክፍል ከመውጣቱ በፊት እጁን መታጠብና የግል መከላከያ መሣሪያ ያወጣል። በመጓጓዣ ጊዜ ቀጥተኛ ግንኙነት የሚጠበቅ ከሆነ ተገቢውን PPE ይልበሱ።
- የትራንስፖርት መኪናን ፀረ-ተባይ በመርጨት ያጽዱ።

***በተቋሙ ፖሊሲ መሠረት ማውጣቱን ያቋርጡ***

***ቅድሙ ጥንቃቄ ከተቋረጠና ክፍሉ ከጸዳ በኋላ ምልክቱ በ Environmental Services (አከባቢ አገልግሎት) ሠራተኞች እንዲነሳ ይደረጋል።***

**420-582  April 2024 Amharic**

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለማግኘት፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸግራቸው ደንበኞች ወደ 711 (Washington Relay) መደወል ወይም ወደ doh.information@doh.wa.gov ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

Washington State Hospital Association

7/30/2024

Washington State Department of HEALTH